# እንቁ ለጣጣሽ - ምን አመጣሽ ?!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ዞረሽ ዞረሽ - ተሽከርክረሽ፤
ተሞናሙነሽ - ተሽቀርቅረሽ፤
እንደሌለን ፡ እንዳልነበርን፤
አፈር ትቢያ ፡ ጭቃ ለብሰን፤
ምናምንቴ ፡ ከንቱ ሆነን፤
ውልብ ሳንል ፡ በትውስታሽ፤
እኛን ፍቀሽ ፡ ከመዝገብሽ፤
እነ አባባ ፡ እነ እማማን፤
ወንድም ጋሼ ፡ እ'ት ዓለምን፤
ዘመድ አዝማድ ፡ ጎረቤቱን፤
ሁሉን ትተሽ ፡ ሁሉን ረስተሽ፤
ቀን አስልተሽ - ወራት ቆጥረሽ ፤
ዓመት ሞልተሽ - ዘመን አዝለሽ፤
እንቁጣጣሽ ምን አመጣሽ ? ለምን መጣሽ ?!

ምን ትሠሪ ? ምን ትፈጥሪ ?
ምን ታወሪ ? ምን ትነግሪ ?
እኮ ለምን ?! ተናገሪ !!

ለወገኔ ለተራበው፤ በደል ጥቃት ላባዘነው፤
ኑሮ ጨሶ ለሚያጨሰው፤ በ'ንባዎቹ ለሚያጠቅሰው፤
በጎዳና ለሚተኛው፤ ለኔ ብጤ፤ ለሷ ብጤ፤ ለኛ ብጤው፤
እንቁጣጣሽ ምን አመጣሽ ?!
ተጠየቂ እስቲ እንስማሽ !!

መሬት ነጥቀሽ - አርሶ አደሩን፤
ሥራ ነፍገሽ - ላብ አደሩን፤
ለነጥቆ አደር ወለል አርገሽ ፡ በር ከፍተሽ፤
ለዘራፊ፤ ለነጣቂ፤ ለሙሰኞች ፡ አዝርግደሽ፤
ብዙሃኑን አስጨንቀሽ ፡ በኑሮ ጣር አጎሳቁለሽ፤
አንገላተሽ - ገለሽ ቀብረሽ፤
ከደላው ጋር - እያሽቃበጥሽ፤
ቀን አስልተሽ - ወራት ቆጥረሽ፤
ዓመት ሞልተሽ - ዘመን አዝለሽ፤
እንቁጣጣሽ ምን አመጣሽ ? ለምን መጣሽ ?!
ተናገሪ እሲቲ እንሸማሽ ?!
ምን ትሠሪ ? ምን ታወሪ ?
ምን ትፈጥሪ ምን ትነግሪ ?
እኮ ለምን ?! ተናገሪ !!

ለጎስቋሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ፡፡

ጳጉሜ 4 ቀን 2003 ዓ.ም. (September 9/2011)